# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ

ህዳር 13 ቀን 2008 ዓ.ምአዲስ አበባ፡ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በቆዳ ቴክኖሎጂ ዘርፍ አብሮ ለማስራት የሚያስችላቸዉን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ፡

የመግባቢያ ስምምነቱን የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሰ እና በኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትየት በኩል ረዳት ፕሮፌሰር አዲሱ ፈረደ ፈርመዋል፡፡






በስምምነት ፊርማዉ ወቅት ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት ሁለቱ ተቋማት ከረጅምጊዜ በፊት በጋራ የሚያከናዉኗቸዉን ተግባራት የመግባቢያ ስምምነት በሚፈራረም ወጥነት ባለዉ ሜካኩ ለማከናወን ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ ቢሆንምበተለያዩ ምክንያቶች እስከዛሬ ማከናወን ሳይቻል ቆይቷል ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ባልተደራጀ ሜካኩም ቢሆን በጋራ ሲሰራ መቆየቱን ነዉ የጠቆሙት፡፡

ስምምነቱ የኢንስቲትዩቱንና የዩኒቨርሲቲዉን ግንኙነት ይበልጥ እንደሚያጠናክረዉም ነዉ የተነገረዉ፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከረጅምጊዜ ጀምሮ ለቆዳ ኢንዱስትሪዉ ዘርፍ የሰዉ ሀይል በማቅረብ ረገድ ሰፊ ስራ ሲሰራ መቆየቱን የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ ያሁኑ ስምምነትም በተለይ ዩኒቨርሲቲዉ በሚገኝበት አካባቢ ለሚገኙ ኢንዱስትሪዎች ብቁ የሰዉ ሀይል በዘርፉ ለማቅርብ እንደሚረዳ ጠቁመዋል፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አዲሱ ፈረደ በበኩላቸዉ ከአሁን በፊት ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪዉ በየፊናቸዉ ሲጓዙ እንደነበረ አስታዉሰዉ፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን ተቀራርበ

የማስራት አዝማሚያ በስፋት እየታነዉ ብለዋል፡፡ ይህም ሁሉም ወገን ጋር ያለዉን ሀገራዊ አቅም በጋራ ለማጠቀም ያስችላል ነዉ ያሉት፡፡

በመግባቢያ ስምምነቱ በጋራ ለማስራት ከስምምነት የተደረሰባቸዉን ጉዳዮች በቁርጠኝነት ለመተግበር በዩኒቨርሲቲዉ በኩል ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለም ጠቁመዋል፡፡

በመግባቢያ ስምምነቱ ማሰረት ሁለቱ ተቋማት በምርምር ፣ በትምህርትና ስልጠና ፣ በስርዓተ ትምህርት ቀረፃ እና በማሰሰሉት ዘርፎች በጋራ የሚሰሩ ሲሆን ይህም የኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ ትስስርን ለማጠናከር ያግዛል ነዉ የተባለዉ፡